በኢትዮጵያ ፌዴራላዊዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

የኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2015 ዓ/ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጁ፣ ደንቡ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዓለም አቀፍ ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ፣ አጥጋቢ ማረጋገጫና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ በሪፖርቱ ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ይሁን የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ወስዶ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተዘጋጁ የሂሳብ ሪፖርቶች፡-

- የሂሳብ ማመዛዘኛ ፣
- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የካፒታል ወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የሚኒስቴሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የአባይ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤቱ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥሮችና ቀናቶች በድምሩ ብር 25,373.09 የጽ/ቤቱ ላልሆኑ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ የተቀዳላቸው፤ ጥገና የተደረገላቸው እና አንድ ተሽከርካሪ የሦስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የተከፈለለት መሆኑ፣
2. የአባይ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤቱ በድምሩ ብር 17,569.20 በነቀምት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለዋናው ጽ/ቤት ወይም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሰራተኛ ላልሆኑ የውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፣
3. የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤት የሀዋሳ ሀይቅን ከብክለት ለመከላከል በተዘጋጀው ስልጠና ላይ ለተሳተፉ ባለድርሻ አካላት ጽ/ቤቱ ውሎ አበል ብር 41,990.00 የከፈለ ሲሆን ለተከፈለው ውሎ አበል ማስረጃ የሚሆን ባለድርሻ አካላቱ በስልጠና ላይ እንዲሳተፉ የላኳቸው የግለሰቦች ስም እና የደመወዝ መጠን የሚገልፅ የመገባጠሚያ ደብዳቤ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ያልቀረበ መሆኑ፣

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

I. ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)

1.1 የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሂሳብ አያያዝ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በድምሩ ብር 11,118,832.50 እንዲሁም
- በአባይ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤቱ ብር 9,638.00

በአጠቃላይ ብር 11,128,470.50 በትክክለኛው ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ክፍያ መፈጸም ሲገባው ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣

1.2 በ2010 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች የሚደረጉ የወጪ ቅነሳ መመሪያ በተራ ቁጥር 7. የመስተንግዶ ወጪን በተመለከተ በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ የመስተንግዶ ወጪዎች በአግባቡ በ መፈተሽ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ በተራ ቁጥር 13. ስልጠና እና ስብሰባን በተመለከተ ከዚህ በፊት የተደረጉ ስልጠናዎች እና ስብሰባዎች ያስገኙትን ውጤት በመገምገም አስፈላጊ የሆኑ ስልጠናዎችን ስብሰባዎችን በመለየት ስልጠናው እና ስብሰባውን በማካሄድ ወጪን መቀነስ ያስፈልጋል ከዚህ ውጭ በአዲስ አበባ ሰብሰባ ሲካሄድ በህግ ከተፈቀደው ውጭ ወጪ መፈፀም ክልክል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለስልጠና ውሎ አበል፣ ለትራንስፖርት እና ለመስተንግዶ በጠቅላላ ብር 1,158,075.28 ከከተማ ውጪ በማሰልጠን የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

1.3 የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤት

- የአርሲ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ስራ አከናውኖ ዉጤቱን እንዲያቀርብ በተዋዋለው መሰረት ብር 524,939.90 የምርምሩ ዉጤት የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በድምሩ ብር 173,000.00 ለመኪና ኪራይ አገልግሎት የዋጋ ማቅረቢያ ያቀረቡት ተወዳዳሪዎች ዋጋ ሞልቶ ያቀረቡበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- የላይኛው አዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤት ለቀን ሰራተኞች ብር 122,930.00 የተከፈለ ቢሆንም፤ ስራው እንዲሰራ የጠየቀ ክፍል ሳይኖር፤ ስራው በትክክል ስለመሰራቱ ያረጋገጠው እና በተረጋገጠው መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም የታዘዘበት ማስረጃ ሳይቀርብ

በአጠቃላይ ብር 820,869.90 ለተከፈለው ክፍያዎች መቅረብ ያለበት ማስረጃዎች ተሟልቶ ሳይቀርቡ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

1.4 በልዩ ልዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት በድምሩ ብር 60,192,180.06 እና ከካፒታል በጀት በድምሩ ብር 892,347,787.29 በአጠቃላይ ብር 952,539,967.35 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ

በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

II. <u>የህጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Matters)</u>

2.1 የአረንጓዴ አሻራ መዝጊያ ፕሮግራም ላይ የመድረክ ስራ የአገልግሎት ግዥ በመፈጸም በድምሩ ብር 1,697,000.00 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በመመሪያው መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 110,673.91 ቀንሶ ያላስቀረና ለታክስ ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ ያላደረገ መሆኑ፣

2.2 የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ክፍል 7 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 28.5 እንዲሁም በፊደል ሐ/ የግንባታ ስራው ሲጠናቀቅ እና ጊዜያዊ ርክክብ ሲደረግ በዚህ አንቀፅ በፊደል ለ/መሰረት ከተያዘው ገንዘብ ላይ 50% ለስራ ተቋራጩ ይለቀቃል ቀሪው 50% ለአንድ አመት የዋገና ጊዜ ተይዞ እንደሚቆይ መመሪያው ላይ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴሩ ለሚያሰራው የግንባታ ስራ ክፍያ ሲፈጽም በመመሪያው መሰረት ከሚፈጽመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ለግንባታ ለስራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን በመያዣ መልክ ተቀንሶ በተከፋይ በመመዝገብ ብር 12,817,269.80 መያዝ ሲገባው ያልቀነሰ መሆኑ ፣

2.3 በጠቅላላው የብር 4,107,871.79 የገበያ ጥናት ሳይደረግ እና በኤጀንሲው ድረ-ገፅ ከሚወጣው ወቅታዊ ዋጋ ጋር ሳይመሳከር በዋጋ ማወዳደሪያ የተገዛ መሆኑ፣

2.4 በጠቅላላው የብር 5,528,916.49 የተገዙ ዕቃዎች በተፈላጊው ባህሪ ዝርዝር መሠረት መቅረቡን በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ገቢ ተደርጎ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ፣

2.5 ሚ/ሩ በብር 200,000.00 የአበባ መትከያ ከኢትዮ ጋርደን ሶልዩሽን ኢንተርፕራይዝ ግዥ እና የአባይ ተፋሰስ በብር 70,000.00 የአዳራሽ ጠረጴዛ ከትዕግስት ገብሩ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ግዥ በድምሩ ብር 270,000.00 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል/19 ያልተቆረጠለት መሆኑ ፣

2.6 ከመደበኛ በጀት በሂሳብ መደብ 2211107 ብር 6,070.15 ከበጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ፣

2.7 በወቅቱ ተሰብስቦ ሂሳቡ መወራረድ ያለበት በአጠቃላይ ብር 304,493,159.64 እስከ ሰኔ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ በሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታይ እና በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

2.8 በወቅቱ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው በአጠቃላይ ብር 12,323,848.47 ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቱ ተከፍሎ ያልተወራረዱ ሂሳቦች መኖራቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

III. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

3.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለማካሄድ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ውል ገብቶ ለተሰራው ሥራ

- የጥናትና ምርምር ስራዎች ልምድ ያላቸው ተመራማሪዎች ስለሚያስፈልግ ይህን ጥናትና ምርምር እንዲያጠኑ የተመረጡ ተመራማሪዎች በምን አይነት መስፈርት እንደተመረጡ ወይም የጸደቀ ስታንዳርድ የውስጥ መመሪያ የሌለ መሆኑ፣
- ተመራማሪዎች ለጥናትና ምርምሩ የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን (cost break down) በሚያቀርቡበት ጊዜ የቀረበው የገንዘብ

መጠን ተገቢነት የሚገመገምበት ወጥ የሆነ የጸደቀ ስታንዳርድ ወይም የውስጥ መመሪያ የሌለ መሆኑ፣

- ይህ ጥናትና ምርምር ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚፈልገው መንገድ እየተሰራ ስለመሆኑ በመሥሪያ ቤቱ በኩል የሚከታተል ኮሚቴ ያልተዋቀረ መሆኑ

በኦዲት ወቅት ለማየት ችለናል፡፡

3.2 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመመሪያው መሰረት ሰራተኞች የሚጠቀሙባቸው መደበኛ ስልኮች የሥራ አመራሩ ወርሃዊ የስልክ ጣሪያ ተመን የሌለው መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3.3 <u>የንብረት አያያዝን በተመለከተ</u>

<u>**የቋሚ ግምጃ ቤትን በሚመለከት**</u>

- በላይኛው አዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤት በጽ/ቤቱ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ ብዛት ያላቸው ዴስክ ቶፕ፣ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-1457 ሞተር ሳይክል ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችለው ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ያልተደረገ እና መወገድ የሚገባቸው እንዲወገዱ ያልተደረገ ንብረት የሚገኝ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረገግጣል፡፡
- በታችኛው አዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽ/ቤት
  - የቋሚና የአላቂ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፡-
  - ኢት 4-08873 ቶዮታ ዳብል ፒክአፕ የሆነ ተሽከርካሪ ሊብሬው በጽ/ቤቱ የሚገኝ ቢሆንም ተሽከርካሪው በአካል የሌለና የት እንዳለ የማይታወቅ መሆኑ፤
  - አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች (የውሃ ቦቴ፣ merchadse Nissan Patrol excavator; loader; dozer; oil filter; universal join(spider kits) dis cover leaf spring) ጎማ በሜዳ ላይ ለአቧራ፣ ለፀሐይ እና ለዝናብ ተጋልጦ የተቀመጡ ሲሆን

አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው የኦዲት አስተያየት በተደጋጋሚ ቢሰጥበትም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፡-

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ አምቼ የሚገኝ የኤሌክትሮኒክስ (ሶላር ክፍል) ውስጥ፣
    - ብዛታቸው 37 የሚሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ (የተበላሹ) ሶላሮች አገልግሎት ከሚሰጡት ንብረቶች ጋር ተቀላቅሎ የሚገኝ መሆኑ፣
    - የንብረት መደርደሪያ ሼልፍ ባለመኖሩ ንብረቶቹ ለቁጥጥርና ክትትል በማያመች ሁኔታ ሜዳ ላይ ተበታትነው የሚገኝ መሆኑ፣
    - እንዲወገዱ የተለዩ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች በግምት ከ20 ዓመት በላይ በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጠው ሳይወገድ የሚገኝ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለማየት ችለናል፡፡

<u>አላቂ ግምጃ ቤትን በሚመለከት</u>

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸው በርክክብ የመጡ አገልግሎት የማይሰጡ (የሚወገዱ) የተለያዩ ንብረቶች ገቢና የወጪ ደረሰኞች፣ ማህተሞች፣ ቅፆች፣ ሃርድ ዲስኮች እና ሌሎች ንብረቶች በአንድ ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆናቸው፣

<u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች</u>

<u>የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

<u>የ2013 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች</u>

- ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሁለት ሰራተኞች ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት ደመወዝ ብር 2,158.81 የተጣራ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፣</u>

- ሶስት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት የተጣራ ደመወዝ በጠቅላላው ብር 7,211.43 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣

<u>የ2010 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፣</u>

- ለተለያዩ ስምንት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት ደመወዝ በጠቅላላው ብር 19,371.57 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣

- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ2010 በጀት ዓመት ከገቢዎችና ግምሩክ ባልሥልጣን በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ አከናውኗል፡፡ ሆኖም
- አቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው ከወጪ ሂሳቡ ጋር የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያያዝ ባለመደረጉ ብር 22,061,557.57 ቀረጥ የተከፈለባቸው እቃዎች ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

የ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

- ከሥራ ገበታቸው ለተሰናበቱ ሶስት ሠራተኞች በጠቅላላው ብር 1,421.80 የደመወዝ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለከሰም ግድብና መስኖ ግንባታ በክፍያ ሰርተፍኬት ቁጥር 46 እና 50 ቀርቦ ክፍያ ሲፈጽም ከግንባታው ወጪ በተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ክፍያና ለፌዴራል ፖሊስ የምግብ አበል (Allowance) በ2008 በጀት አመት ብር 826,547.85 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለብር 596,311.30 ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን ለብር 230,236.55 ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤
- አራት ሰራተኞች ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ብር 5,688.20 የደመወዝ እና የመንግሥት የጡረታ መዋጮ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- ታህሳስ 26 ቀን 2008 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 02/7/321 በተጻፈ ደብዳቤ ከሀምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ወደ አባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን ለተዛወሩ ሰባት ሰራተኞች ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ ደመወዝ እንዳይከፈላቸው የሚያመለክት ቢሆንም ለሰራተኞቹ ከሀምሌ 2007 ዓ.ም እስከ ህዳር 2008 ዓ.ም ድረስ የ5 ወር ደመወዝ እና የመንግሥት የጡረታ መዋጮ ክፍያ ብር 73,781.15 የተፈጸመ እና ከዚህ ውስጥ ከአምስት ሰራተኞች ብር 21,703.43 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 52,077.72 ተመላሽ ያልተደረገ እና ለሥራ ግብሩና ለጡረታ ተቀናሹ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለከሰም ግድብና መስኖ ግንባታ የክፍያ ሰርተፍኬት ቁጥር 46 እና 50 ቀርቦ ክፍያ ሲፈጽም ከግንባታው ወጪ በተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ክፍያና ከ2008 በጀት ዓመት በፊት ከብር 4,161,016.74 ውስጥ ቀሪ ብር 1,913,050.58 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ግኝቶች፤

- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከጥር 4 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ጥር 9 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ እንዲሁም ከጥር 13 ቀን 2007 ዓ.ም እስከ ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ በአዳማ ድሬ ኢንተርናሽናል ሆቴል ወርክሾፕ ባካሄደበት ወቅት እንደመጡበት አካባቢ በጠቅላላው ብር 176,009.00 የውሎ አበል እንዲከፈል የተደረገ ቢሆንም:- ለተመሳሳይ ቀናት በድጋሚ ብር 172,430.00 የውሎ አበል ክፍያ በመፈጸሙ፤ ለሁሉም የስልጠና ተሳታፊዎች ለስድስት ቀን የምሳ አበል የተሸፈነ ሆኖ ሳለ በተጨማሪ ብር 35,037.00 የውሎ አበል ክፍያ በመፈጸሙ፤ በጠቅላላው አለአግባብ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ብር 207,467.00 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠና በተጨማሪም የስብሰባ ተሳታፊዎች ገንዘቡን ሳይቀበሉ ሁለት ጊዜ እንዲፈርሙ ተደርጎ ገንዘቡ ወጪ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ሁኔታው በውስጥ ኦዲት ክፍሉ አማካኝነት እንዲጣራ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የኦዲት ክፍሉ ሁኔታውን አጣርቶ አንደኛው ክፍያ ለውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ሁለተኛው ክፍያ ደግሞ ለአልጋ ተብሎ እንዲከፈል የተደረገ መሆኑን ሚያዚያ 11 ቀን 2008 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት መሰረት ብር 14,943.50 ብቻ ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ብር 192,523.50 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

የ2006 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

- አቶ በሃይሉ ግርማ የተባሉ በአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ልማት እና ሽግግር ዳይሬክቶሬት ሥር ይሰሩ የነበሩ ሰራተኛ ህዳር 10 ቀን 2006

ዓ.ም ደብዳቤ ቁጥር ሠበ1/9/8 መሥሪያ ቤቱን ለመልቀቃቸው በሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት የተጻፈና ለግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግልባጭ የተደረገ ቢሆንም ላልሰሩበት ቀን ከኅዳር 11 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ኅዳር 30 ቀን 2006 ድረስ ያለው የ20 ቀን ደመወዝ ብር 1,499.00 ያለአግባብ ተከፍሎአቸው የተገኘ መሆኑ፤

የቀድሞው ኢነርጂ ባለሥልጣን የ2013 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

- በሚች አቶ ይስሃቅ አያና የሶስት ወር ደመወዝ ብር 22,068.00 መከፈል ሲገባው ብር 27,168.00 በመከፈሉ ምክንያት በብልጫ ብር 5,100.00 በአካውንታቸው ገቢ የተደረገ መሆኑ፤

የቀድሞው የውሃ ልማት ኮሚሽን የ2012 ዓም የኦዲት ግኝቶች፤

- ከብሪጅቴክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በብር 15,198.01 ፕሪንተር ተገዝቶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በመዝገብ የተመዘገበውና ሪፖርት የተደረገው ግን ብር 10,128.01 ብቻ በመሆኑ ብር 5,064.00 በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መሆኑ፤
- ከአልታ ኮምፒዩቴክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በብር 251,780.01 ፎቶ ኮፒ ማሽን ተገዝቶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በመዝገብ የተመዘገበውና ሪፖርት የተደረገው ግን ብር 261,908.02 በመሆኑ ብር 10,128.01 ያለአግባብ በብልጫ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤

የቀድሞው ስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የ2013 ዓ.ም የኦዲት ግኝቶች፤

- ከፋኑኤል የዕጽዋት ዘር አቅራቢ ድርጅት ጋር የብር 548,300.00 ዋጋ ያላቸው የችግኝ መትከያ ፖሊቲን ለማቅረብ ጨረታ አሸንፎ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ አንቀጽ 3 መሰረት ውል ተቀባይ እስከ የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ዕቃዎቹን አጠናቆ ገቢ ማድረግ ያለበት ቢሆንም ድርጅቱ የብር 193,047.85 ንብረት ብቻ ገቢ ያደረገ ቢሆንም ቀሪውን የብር 355,252.15 ንብረቶችን ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤

የ2012 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

- ጽህፈት ቤቱ የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር የምክክር ፎረም በሀዋሳ ከተማ ባዘጋጀበት ወቅት ለተሳታፊዎች በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር CPV 462478 የውሎ አበል ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ስብሰባው የተካሄደው ከጥቅምት 3 እስከ ጥቅምት 4 ቀን 2012 ዓ.ም ሁለት ቀን ሲመጡና ሲሄዱ በጠቅላላው የአራት ቀናት የውሎ የወሎ አበል ክፍያ መፈጸም ሲገባው የ6 ቀን የውሎ አበል በመፈጸሙ ምክንያት አለአግባብ የከፈለው ብር 8,000.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ጽህፈት ቤቱ በዲላ ከተማ አስተዳደር የእንቦጭ ወራሪ አረምን የመቆጣጠርና የማስወገድ ሥራ ላይ ምክክር ለማድረግ ከጥር 19 እስከ 20 ቀን 2012 ዓ.ም በተዘጋጀ ስብሰባው ለሁለት ቀናት እንዲሁም የስብሰባው ተሳታፊዎቹ ሲመጡና ሲሄዱ ለሁለት ቀናት በጠቅላላው የአራት ቀናት የውሎ የወሎ አበል ክፍያ መፈጸም ሲገባው የ7ቀን የውሎ አበል በመፈጸሙ ምክንያት አለአግባብ የተከፈለው ብር 19,818.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች የነበሩ 8 ግለሰቦች በዝውውር ምክንያት ወደ ተፋሰሶች ልማት ባለሥልጣን እና አዋሽ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት ሲሄዱ ይገለገሉበት የነበረውን ብር 118,302.37 ዋጋ ያላቸው ቋሚ ንብረቶችን ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ፤

የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

- የተፋሰስ ውሃ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በንኡስ ተፋሰስ ውስጥ ለሚገኙ ትልልቅ የውሃ ተጠቃሚዎችን የውሃ አጠቃቀም አያያዝና ብክለት ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባው የተካሄደው ጥር 17/2011 ለአንድ ቀን ቢሆንም ጽህፈት ቤቱ መፈጸም ካለበት የውሎ አበል ክፍያ በላይ አላግባብ የከፈለው ብር 31,499.10 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ጽህፈት ቤቱ ከታህሳስ 26 እስከ 27 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር የዩኒቨርስቲ ትስስር ፎረም የምክክር መድረክ በአበበ

ዘለቀ ኢንተርናሽና ሆቴል ባዘጋጀው ስልጠና ተሳታፊዎቹ የቆዩበት ሁለት ቀን ብቻ ቢሆንም ጽህፈት ቤቱ መፈጸም ካለበት በላይ አላግባብ የከፈለው ብር 63,149.50 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ ላለው ጊዜ ከፈጸመው የስልክ አገልግሎት ክፍያ ውስጥ ብር 10,545.74 ከኢትዮጵያ ዉጪ ለግል ጉዳይ ዩናይትድ አረብ ኢሚሬት፣ ሊባነን እና ኔዘርላንድ በተደጋጋሚ የተደወለበትና የቴክስት መልእክት ለተላከበት የተፈጸመ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ጽህፈት ቤቱ በወላይታ ሶዶ ከተማ የዩኒቨርስቲ ትስስር ፎረም የምክክር መድረክ ባዘጋጀበት ወቅት 8 ባለሙያዎች ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ መጥተው ጥናታዊ ጹሁፋቸውን ያቀረቡ ሲሆን ግለሰቦቹ ምንም እንኳ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቢያቀርቡም የንግድ ፍቃድ ስላላቀረቡ በጠቅላላው ከተፈጸመው ክፍያ ብር 28,500.00 ላይ 30% የገቢ ግብር ብር 8,550.00 መሰብሰብ ሲገባው 2% ብር 570.00 ብቻ በመሰብሰቡ ምክንያት ብር 7,980.00 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
- ኅዳር 2 ቀን 2008 ዓ.ም የጽህፈት ቤቱ ሥራ አመራር አባላት መሥሪያ ቤቱ ለገዛቸው ሞተር ሳይክሎች የሚሰጠው ቤንዚን እንዲወሰን በቀረበው ሃሳብ መሰረት ለሞተር ሳይክል ተጠቃሚዎች በወር 15 ሊትር ቤንዚን እና 1 ሊትር ዘይት ተገዝቶ እንዲሰጥ በተወሰነው መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለሁለት ሰራተኞች የ30 ሊትር ቤንዚን እና 2 ሊትር የሞተር ዘይት መግዣ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 462368 ተከፍሎ ሂሳቡ እንዲወራረድ በመደረጉ ምክንያት ብር 1,250.70 አለአግባብ ወጪ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑ፤
- የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ለመስክ ስራ በናሆም የመኪና ኪራይ ወደ ተለያየ ስፍራ የተንቀሳቀሱ መሆኑ ቢታወቅም ግለሰቦቹ ለስራ የቆዩበት ቀናትን ከመኪና ኪራይ ክፍያ ለመረዳት ቢቻልም በጠቅላላው መስክ

ከቆዩበት ቀናት በላይ በብልጫ የተከፈላቸው ብር 28,269.40 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ጽህፈት ቤቱ በተፋሰስ ደረጃ የተፋሰስ እቅድ (Basin plan) ዝግጅት ላይ ሃያ ስምንት የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች እና ሁለት የአርሲ እና የወላይታ ዩኒቨርስቲ ሙሁራን ከሚያዝያ 14 ቀን 2011 እስከ ግንቦት 13 ቀን 2011 ድረስ ለሰላሳ ቀን የእቅድ ዝግጅቱ ላይ የተሳተፉ ሲሆን ለሴንትራል ሃዋሳ ሆቴል ከተፈጸመው የውሃ አቅርቦትና የሪፍሬሽመንት አገልግሎት ክፍያ መረዳት ቢቻልም በአዋሳ ሴንትራል ሆቴል ስብሰባ ላይ በነበሩበት ወቅት በተለያዩ ቦታዎች መስክ እንደነበሩ በማስመሰል ያለአግባብ የተፈጸመው ብር 39,230.00 የውሎ አበል ክፍያ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ጽህፈት ቤቱ ለወ/ሮ የትነበርሽ ይታየው ከመስከረም 2011 እስከ ግንቦት 2011 ድረስ ያለውን የደመወዝ ልዩነት ክፍያ ሲፈጽም ብር 1,339.15 የሥራ ግብር ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

የ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

- ጽህፈት ቤቱ በሀዋሳ ሀይድሮሎጂ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እና በማዕከላዊ የሀይድሮሎጂ ጣቢያዎች የሚሰሩ የሰራተኞች ዝርዝር የሰው ኃይል እና የክፍያ መጠንን አስመልክቶ ከኢፌድሪ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ጋር ሐምሌ 11 ቀን 2008 ዓ.ም በቃለ ጉባኤ በቁጥር ውመአሚ66/10/281 ርክክብ ፈጽሟል፡፡ ነገር ግን ከሀምሌ ወር 2008 እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ለሰሩበት ክፍያ ሲፈጸም በየትኛው ጣቢያ እንደሚሰሩ ያልታወቁና ውል ላልተገባላቸው ሰዎች ብር 45,600.00 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
- የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለመጎብኘት ሲሄዱ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ላልሆኑ አቶ ኃይሉ አርቃ እና አቶ እሸቱ ቦልካ ለተባሉ ግለሰቦች በጠቅላላው ብር 6,242.00 የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

- ጽህፈት ቤቱ በኖክ ካርድ በብር 300,000.00 የነዳጅ ግዥ የፈጸመ ሲሆን፣ ነዳጁ አገልግሎት ላይ ለመዋሉ ማስረጃ እስኪቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲያዝ በተሰጠው ማሳሰቢያ መሰረት ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በሂሳብ ማዘዣ ቁጥር 87827 በአቶ አስመላሽ አበባየሁ ስም በተሰብሳቢ እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን በማደያው ውስጥ ምንም ነዳጅ የሌለ መሆኑን በቀረበው የኖክ ነዳጅ ማደያ ድርጅት ያሳወቀበት ሊስት ለመረጃ የቀረበ ቢሆንም ነዳጁ የመሥሪያ ቤቱ ንብረት ለሆኑት መኪኖች ስለመሞላቱ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ከላይ የተጠቀሰውን የቀድሞ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ የሆኑትን ሃዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሶ የካቲት 16 ቀን 2010 ዓ.ም ለጽህፈት ቤቱ የፍርድ ውሳኔ በተሰጠው መሰረት ከተከሳሹ ዋስ ላይ በየወሩ እየተቀረጠ በ2012 በጀት ዓመት ብር 10,532.96 እንዲሁም በ2013 በጀት ዓመት ብር 19,467.04 በድምሩ ብር 30,000.00 ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 270,000.00 ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣

<u>**በቀድሞ አባይ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች**</u>

- የአባይ ተፋሰስ ልማት ጽህፈት ቤት አካል በሆነው አሶሳ ቅርንጫፍ ከሰኔ 27 ቀን 2011 እስከ ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም በአለም አቀፍ ደረጃ በሰፊው በመተግበር ላይ ያለውን የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር መርሆዎች ለመተግበር የሚያስችል ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የተቀናጀ የተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት የምክክር መድረክ በአሶሳ ከተማ በብሌንዳና ሆቴል ባዘጋጀው ወርክሾፕ ላይ ተሳታፊዎቹ በስብሰባው ላይ ለቆዩበት ጊዜና በተጨማሪም ከተለያየ ክልሎች ለመጡ ተሳታፊዎች በመንገድ ላይ ለሚያሳልፉት ጊዜ እንደመጡበት አካባቢ የወሎ አበል ክፍያው ታሳቢ ተደርጎ ሲታይ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 806957 የፈጸመው ክፍያ ሆቴሉ ከሰጠው መስተንግዶና ጽህፈት ቤቱ

ፕሮፎርማ ሲሰበስብ ለድርጅቶቹ ካሳወቀበት ደብዳቤ እንዲሁም ከመገጣጠሚያ ደብዳቤው መረዳት እንደሚቻለው ስብሰባው የተካሄደው ከሰኔ 27 ቀን 2011 እስከ ሰኔ 28 ቀን 2011 ድረስ ለሁለት ቀን ቢሆንም ጽህፈት ቤቱ መፈጸም ካለበት የውሎ አበል ክፍያ በላይ ብር 34,952.70 ሰብሰባው ከተካሄደበት ቀን በላይና ስብሰባው ከተካሄደበት ከአሶሳ ከተማ የአበል ተመን ዉጪ አለአግባብ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

የ2010 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች

- የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ ሰራተኛ የሆኑት አቶ አንድነት ዘላለም መላኩ ከ2008 እስከ ነሀሴ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ መሥሪያ ቤቱ ሰራተኛ በሆኑና ባልሆኑ ግለሰቦቹ ሥም የመስክ ሥራ እንደወጡ በማስመሰል ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባህርዳር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አለአግባብ ወጪ የተደረገው ሂሳብ ብር 605,956.64 በባለሥልጣን የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የተረጋገጠ መሆኑ ተገልጾ ይሄው በውስጥ ኦዲት የተሰራው ሥራ ታይቶ አስተያየት እንዲሰጥበት በተጠየቀው መሰረት ሲጣራ አለአግባብ ወጪ ተደርጓል ተብሎ ከላይ ከተገለጸው ገንዘብ ውስጥ በ2010 በጀት ዓመት የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ላልሆኑ 4 ግለሰቦች ለምን ሥራ ጉዳይና ከየት እንደመጡ የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር የውሎ አበል ክፍያ ብር 21,708.30 እንዲሁም 6 የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ደግሞ የመስክ ሥራ ሳይወጡ ለመስክ ሥራ እንደወጡ በማስመሰል ብር 33,791.30 በድምሩ ብር 55,499.60 በመሥሪያ ቤቱ በሚዘጋጀዉ የባንክ ወጪ ሰነድ እና በቀሪው ጉርድ ቼክ ላይ ግለሰቦቹ እንደወሰዱ ተደርጎ ሥማቸው የተጻፈ ቢሆንም ከባንክ ገንዘቡን በቼክ ወጪ ያደረገዉ ግን ሂሳቡን ያዘጋጀዉ የሂሳብ ሰራተኛ አቶ አንድነት ዘላለም መሆኑን ከባንክ በተላከ ማረጋገጫ መሰረት በውስጥ ኦዲት ሪፖርት የተረጋገጠው ሂሳብ ትክክለኛ መሆኑ ተገልጾ ግለሰቡ ለፈጸሙት
-

ተገቢ ያልሆነ ተግባር በህግ አግባብ እንዲጠየቁ እና ያለአግባብ ወጪ የተደረገው ገንዘብም በአስቸኳይ እንዲመለስ መደረግ ተብሎ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በፍርድ ውሳኔው መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

ተገልጾ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ባለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ ኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት 2015 ዓ.ም